# እርዳታ፡
# ከላይ



አዘጋጅ፤ ዋትሰን፡ጉድማን

የማይሸጥ፡ በነፃ፡የሚታደል።

"ኢርዳታ፡ከሳደ፡" በአርእስት፡ተዛማጅ፡የሆኑ፡
ቅዱስ፡ጥቅሶች፡ከልዩ፡ልዩ፡ከመጽሐፍ፡ቅዱስ፡
ክፍሎች፡በማውጣጣት፡የተዘጋጁ፡ነው።በእኔ፡
እምነት፡ከሁሉ፡የተሻለ፡የቅዱስ፡ቃላቶች፡
መግለጫ፡መጽሐፍ፡ቅዱስ፡ነው።
የእግዚአብሔር፡ቃል፡የሚመጣው፡"ከሳደ"፡
ነው።በእርግጥም፡ልገቻው፡ለበጎ፡ሥራ፡
ለሚራብና፡ለሚጠማ፡በጣም፡ይረዳል።
እንደ፡ሰው፡ሲፀፀት፤ከሐጢአት፡ሲርቅ፤
ጌታ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በልቡ፡እንዲያድር፡
ሲለምን፤በሙሉ፡ልቡ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡አዳኙ፡መሆኑን፡ሲያምን፤
ለዚህ፡ሰው፡ጌታ፡ሰላቱንና፡የሰላቱንም፡ዳስታ
ና፡ሰላም፡በአማኙ፡ልብ፡ያሳድራል።እኔ
ም፡ደህን፡ፀጋ፡በ1930፡ዓ፡ም፡ተቀበልሁ።
ከዚያንም፡ጊዜ፡ጀምሮ፡ደህንን፡ማሬም፡
ግንኙነት፡ከጌታዬ፡ጋር፡አሳቋረጥኩም።
እርስዎም፡እስካሁን፡ጌታን፡አዳኝዎና፡ጌታዎ፡
አድርገው፡ያልተቀበሉ፡ከሆነ፡አሁኑኑ፡ለሱ
ዎን፡ለሱ፡እንዲሰጡ፡በማቻኮል፡እሳስ
ብቃታለሁ።

ቀቶሰን፡ጉጽማን፡

# የእግዚአብሔር፡ ፍቅር።

## የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፫፥

፲፮፥ እግዚአብሔር፡ እንዲሁ፡ ዓለሙን፡ ወድዋል
ና፡ አንድ፡ ልጁን፡ እስኪሰጥ፡ ድረስ። በርሱ፡ ያመነ፡
ሁሉ፡ እንዳይጠፋ፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ ትሆንለት፡
ዘንድ፡ እንጂ።

## ፩፡ ዮሐንስ። ፬፥

፰፥ የማይወድም፡ እግዚአብሔርን፡ አላወቀም።
እግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ነውና።
፱፥ በዚህ፡ ተገለጠ፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ወደ
ኛ፡ እግዚአብሔር፡ አንድ፡ ልጁን፡ ወደ፡ ዓለም፡ ልኳ
ልና፡ በርሱ፡ እንድንበት፡ ዘንድ።

## ትንቢተ፡ ኤርምያስ። ፴፩፥

፫፥ እግዚአብሔር፡ ከሩቅ፡ ተገለጠልኝ፡ አለም።
በዘላለም፡ ፍቅር፡ ወደድሁሽ፡ ስለዚህም፡ በርኅራኄ፡
ሳብሁሽ።

## የዮሐንስ፡ ራእይ። ፩፥

፭፥ ከየሱስ፡ ክርስቶስም፡ ከታመነው፡ ምስክር።
የሙታን፡ በኵር፡ የምድር፡ ነገሥታትም፡ አለቃ።
ለወደደን፡ ከኃጢአታችንም፡ በደሙ፡ ላጸበን።

# የጌታ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡
# መለኰትነት ።

## የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፬፤

፱፤ አለው፡የሱስ። እኔ፡ ከላንተ፡ጋራ፡ነኝ፡ይህነን፡ ያ
ህል፡ዘመን፡አታውቀኝምን፡ፊልጶስ። እኔን፡ያየ፡አብ
ን፡ፈጽሞ፡ አየ ። እንዴትም፡ ትላለህ ፡ አንተ፡ አብን፡
አሳየነ።

፲፤ አታምንምን፡ እኔ፡ በአብ፥ እንዳለሁ፡ አብም፡
በኔ። ለላንት፡ የምነግራችሁን፡ ነገር፡ ከኔ፡ አልነግርም።
አብ፡ በኔ፡ ያደረብኝ፡ እርሱ፡ ስራውን፡ ይሰራል፡ እን
ጂ።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፩፤

፳፪፤ ይህም፡ ሁሉ፡ ሆነ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡
በነቢይ፡የተባለው፡ሊፈጸም፡የሚል።
፳፫፤ እነሆ፡ ድንግል፡ ትፀንሳለች፡ ልጅም፡ ትወልደ
ለች፡ ስሙንም፡ አማኑኤል፡ ይሉታል፡ ትርጓሜው፡
እግዚአብሔር፡ ከኛ፡ ጋራ፡ የሆነ።

## ወደ፡ ጢሞቴዎስ፡ ፩። ፫፤

፲፮፤ በውነትም፡ ታላቅ፡ ነው፡ የአምልኮት፡ ምሥ
ጢር። አምላክ፡በሥጋ፡ተገለጠ።በመንፈስ፡ ጸደቀ።
ለመላእክት፡ ታየ። በአሕዛብ፡ ተሰበከ። ከዓለም፡ታ
መነ። በምስጋናም፡ ታረገ፡ ወጣ።

# ኢየሱስ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ።

## ትንቢት፡ ኢሳይያስ። ፱፡

፮፡ ሕፃን፡ ተወልደልናልና፡ ወንድ፡ ልጅም፡ ተሰ
ጠነ፡ አለቅነቱም፡ በጫንቃው፡ ላይ፡ ይሆናል። ስሙ
ም፡ ድንቅ፡ ተብሎ፡ ይጸራል፡ መካርም፡ ብርቱም፡ አ
ምላክ፡ የዘላለም፡ አባት፡ የሰላም፡ አለቃ።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፲፯፡

፭፡ እርሱም፡ ይህን፡ ሲናገር፡ እነሆ፡ የበራ፡ደመና፡
መጣና፡ ሰወራቸው። ድምፅም፡ ከደመና፡ መጣ፡ እ
ንደ፡ህ፡ ቢል። ይህ፡ ነው፡ የምወደው፡ ልጄ፡ በርሱ፡ ደ
ስ፡ የሚለኝ። እርሱን፡ ስሙት።

## የሉቃስ፡ ወንጌል። ፩፡

፴፭፡ መልአኩም፡ መለሰ፡ አላትም። መንፈስ፡
ቅዱስ፡ይመጣብሻል፡የልዑልም፡ኃይል፡ያጸለልሻል።
ስለዚህም፡ ደግሞ፡ ቅዱሱ፡ ነገር፡ የተወለደው፡ የ
እግዚአብሔር፡ ልጅ፡ ይባላል።

## ፩፡ ዮሐንስ። ፬፡

፲፭፡ የሱስ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ እንደ፡ሆነ፡ የሚ
ያምን፡ እግዚአብሔር፡ ይኖርበታል፡ እርሱም፡ በእግ
ዚአብሔር፡ ይኖርበታል፡ እርሱም፡በእግዚአብሔር።

# ኢየሱስ፡ ማን፡ እንደሆነ፡ ይነግረናል።

### የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፡

፯፡ የሱስም፡ደግሞ፡አላቸው። እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ። እኔ፡የበጎች፡ ደጅ፡ እንደ፡ ሆንሁ።

### የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፰፡

፳፫፡ አላቸውም። እናንተ፡ከታች፡እኔም፡ ከላይ። እናንተ፡ ከዚህ፡ ሓለም፡ እኔ፡ ከዚህ፡ሓለም፡አይደለ ሁም።

### የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፰፡

፶፰፡ አላቸው፡የሱስ።እውነት፡እውነት፡እላችኋለ ሁ።አብርሃም፡ሳይወለድ፡እኔ፡ነኝ።

### የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፩፡

፳፭፡ የሱስም፡አላት።እኔ፡ነኝ፡ ትንሣኤ፡ሕይወት ም።ያመነብኝ፡ ቢሞትም፡ ይድናል።

### የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፮፡

፴፭፡ የሱስም፡ አላቸው። እኔ፡ነኝ፡ የሕይወት፡ እ ንጀራ። ወደኔ፡ የሚመጣ፡ አይራብም። የሚያምን ብኝም፡ አይጸማም፡ ለዘላለም።

### የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፱፡

፭፡ በሓለም፡ሳለሁ፡ እኔ፡ የዓለም፡ ብርሃን፡ ነኝ።

ኢየሱስ፡ ከፈጸማቸው፡
ታምራቶች፡ ጥቂቶቹ ።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፲፬፡

፲፱፡ አሕዛብም፡ በመስክ፡ ላይ፡ እንዲቀመጡ፡ አ
ዘዘ። አምስቱንም፡ እንጀራና፡ሁለቱን፡ዓሣ፡ ወሰደ፡
ወደ፡ ሰማይም፡ አየ፡ ባርከውም። እንጀራውንም፡
ቈረሰ፡ ለደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ለአሕዛብ፡ ሰጡት።
፳፡ ሁሉም፡ በሉ፡ ጠገቡም፡ የተረፈውንም፡ ቍራ
ሽ፡ አነሡ፡ አሥራ፡ ሁለት፡ ሞሰብ፡ መልተው።
፳፩፡ የበሉትም፡ አምስት፡ ሺህ፡ ሰዎች፡ነበሩ፡ ከሴ
ቶችና፡ ከሕፃናት፡ ሌላ።

## የሉቃስ፡ ወንጌል። ፭፡

፬፡ ነገሩንም፡ በፈጸመ፡ ጊዜ፡ ሲሞንን፡ አለው። ወ
ደ፡ ጥልቁ፡ ቅረብ፡ መርበብታችሁንም፡ ለማጥመድ፡
ጣሉ።
፭፡ ሲሞንም፡ መለሰ፡ አለው። መምህር፡ሆይ፡ ሌ
ቱን፡ ሁሉ፡ ፈጽመን፡ ደከምን፡ምንም፡ አልያዝንም።
ነገር፡ ግን፡ በነገርህ፡ መርበብቱን፡ እጥላለሁ።
፮፡ ይህነንም፡ ባደረጉ፡ ጊዜ፡ ካሣው፡ እጅግ፡ ብዙ፡
ወሰደ። መርበብታቸውም፡ ለመቀደድ፡ ቀረበች።

# ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ፈጣሪና፡ ጌታ፡ነው።

ወደ፡ ቆላሳይስ፡ ሰዎች። ፩፡

፲፮፡ ነገር፡ሁሉ፡በርሱ፡ ተፈጥርዋልና፡በሰማያት፡
ያለ፡ሁሉ፡በምድርም፡ያለ።የሚታይ፡የማይታይም፡
መናብርትም፡እጋእዝትም፡ሊቃናትም፡ሥልጣናት
ም።ሁሉ፡በርሱ፡ለርሱም፡ተፈጠረ።

የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፩፡

፫፡ ሁሉ፡ በርሱ፡ሆነ፡ ያለርሱም፡ አልሆነም፡ ምን
ም፡ ከሆነው፡ ሁሉ።

ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፲፬፡

፱፡ ስለዚህም፡ ክርስቶስ፡ ሞተ፡ ተመልሶም፡ ሕ
ያው፡ ሆነ፡ የሕያዋንና፡የሙታን፡ጌታ፡ይሆን፡ዘንድ።

ወደ፡ ዕብራውያን። ፩፡

፪፡ እርሱ፡በዚህ፡በኋለኛው፡ዘመን፡ በልጁ፡ነገረን፡
ሁሉን፡ ወራሽ፡ባደረገው። ዓለሙንም፡በርሱ፡ የፈ
ጠረ።

የሐዋርያት፡ ሥራ። ፪፡

፴፮፡ እንግዲህ፡በውነት፡ይወቅ፡የእሥራኤል፡ ወ-
ገን፡ ሁሉ። እግዚአብሔር፡ ይህነን፡ የሱስን፡እላንተ፡
የሰቀላችሁትን፡ጌታ፡ መሢሕም፡ እንደደረገው።

# ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ የሁሉ፡ ዳኛ፡ ነው።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፳፭፡

፴፪፡ አሕዛብም፡ ሁሉ፡ በፊቱ፡ ይሰበሰባሉ። እር
ሱ፡ በርሳቸውም፡ ይለያቸዋል፡ ጠባቂ፡ በጎችን፡ከፍ
የሎች፡ እንዲለይ።

## የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፭፡

፳፪፡ አብ፡ በማንም፡ አይፈርድምና። ነገር፡ ግን፡ ፍ
ርድን፡ ሁሉ፡ ለልጁ፡ ሰጠው።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች፡ ፪፡

፲፮፡ ፍርዳቸውም፡ ይሆናል፡ እግዚአብሔር፡ በሰ
ው፡ ምሥጢር፡ በሚፈርድበት፡ ቀን፡ በየሱስ፡ ክርስ
ቶስ። እኔ፡ በወንጌል፡ እንዳስተማርሁ።

## የሐዋርያት፡ ሥራ። ፲፡

፵፪፡ ለሕዝብም፡ እናስተምር፡ እንመሰክርም፡
ዘንድ፡ አዘዘ፤ ይህ፡ እንደ፡ ሆነ፡ እግዚአብሔር፡ የመረ
ጠው፡ በሕያዋንና፡ በሙታን፡ ይፈርድ፡ ዘንድ።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፲፬፡

፲፡ አንተስ፡ ለምን፡ በወንድምህ፡ ትፈርዳለህ።
አንተስ፡ ምንድር፡ ነህ፡ ወንድምህን፡ የምትንቅ።
ሁላችን፡ በክርስቶስ፡ ወንበር፡ ፊት፡ እንቆማለንና።

# መዳን፡ በክርስቶስ፡ በኩል፡ ብቻ።

ወደ፡ ዕብራውያን። ፭፤

፱፤ በተፈጸመም፡ ጊዜ፤ ለሚታዘዙት፡ ሁሉ፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ ተምክንያት፡ ሆነ።

የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፬፤

፮፤ የሱስም፡ አለው። እኔ፡ መንገድ፡ ነኝ፡ እውነትም፡ ሕይወትም። አንድም፡ ወደ፡ አብ፡ አይመጣም፡ በኔ፡ በቀር።

የዮሐንስ፡ ራእይ። ፭፤

፱፤ አዲስ፡ ምስጋናም፡ ያመሰግኑ፡ ነበር፡ እንዲህ፡ ሲሉ። ላንተ፡ ይገባል፡ መጽሐፉን፡ ትወስድ፡ ዘንድ ማሕተሙንም፡ ትፈታ፡ ዘንድ። ታርደሃልና፡ በደምህም፡ ለእግዚአብሔር፡ ገዝተህናልና፡ ከዘመድ፡ ሁሉ፡ ከቋንቋንም፡ ከወገንም፡ ከሕዝብም።

የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፰፤

፳፬፤ ስለዚህም፡ አልኋችሁ፡ በኃጢአታችሁ፡ እንድትሞቱ። እኔ፡ እንደ፡ ሆንሁ፡ ባታምኑ፡ በኃጢአታችሁ፡ ትሞታላችሁና።

የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፡

፱፤ ደጂ፡ እኔ፡ ነኝ። ማንም፡ በኔ፡ የገባ፡ ይድናል፡ ይገባልም፡ ይወጣልም፡ መሰማርያም፡ ያገኛል።

## ወደ፡ ቆላስይስ፡ ሰዎች። ፩፥

፲፪፥ አብን፡ ስታመሰግኑ፡ ለቅዱሳን፡ ርስት፡ መክፈ
ልት፡ በብርሃን፡ ያበጀነውን።
፲፫፥ በጨለማ፡ ሥልጣን፡ ያደነነ፡ ወደ፡ ወደደውም፡
ወደ፡ ልጁ፡ መንግሥት፡ የወሰደነ፡ ተከለነ።
፲፬፥ በርሱ፡ መድኃኒት፡ የተቀበልነ፡ በደሙ፡ የኃጢ
አትን፡ ይቅርታ።

## ወደ፡ ቆሮንቶስ፡ ሰዎች። ፩፡፡ ፩፥

፴፡ እናንተ፡ ግን፡ ከርሱ፡ ናችሁ፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡
ጥበብ፡ የሆነልን፡ ከእግዚአብሔር፡ ጽድቅም፡ ቅድ
ስናም፡ መድኃኒትም።

## የሐዋርያት፡ ሥራ። ፬፥

፲፪፥ በማንም፡ ደህንነት፡ የለም፡ በሌላው። ሌላ፡ ስ
ም፡ የለምና፡ በሰማይ፡ ታች፡ ለሰው፡ የተሰጠ፡ በርሱ፡
ይድን፡ ዘንድ፡ የሚገባ።

## የሉቃስ፡ ወንጌል። ፲፱፥

፲፥ የሰው፡ ልጅ፡ መጥትዋልና፡ የጠፋውን፡ ይሻ፡ ዘ
ንድ፡ ያድነውም፡ ዘንድ።

## ወደ፡ ቲቶስ። ፪፥

፲፬፥ ራሱን፡ ስለኛ፡ የለወጠ፡ ከኃጢአት፡ ሁሉ፡ ያ
ድነነ፡ ዘንድ። ለራሱም፡ የተመረጠ፡ ወገን፡ ያነጻ፡ ዘን
ድ፡ ለመልካም፡ ነገር፡ የሚቀና።

# የክርስቶስ፡ደም፡አዳኝነት።

## ፩፡ ዮሐንስ፡ ፩፡

፯፤ በብርሃን፡ ግን፡ ብንመላለስ፡ እርሱ፡ በብርሃን፡ እንዳለ፡ ለኛ፡ አንድነት፡ አለን፤ እርሱ፡ በርሳችን፡ የል ጁም፡ የየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ደም፡ ከኃጢአት፡ ሁሉ፡ ያነ ጻናል።

## ወደ፡ ኤፌሶን፡ ሰዎች። ፩፡

፯፡ በርሱ፡ መድኃኒት፡ የተቀበልን፡ በደሙ፡ የኃጢ አት፡ ስርየት፡ ከጸጋው፡ ባለጠግነት፡ የተነሣ።

## ፩፡ ጴጥሮስ። ፩፡

፲፰፤ ታውቃላችሁና፡በሚጠፋ፡ በወርቅና፡ በብር፡ ከከንቱ፡ ስራችሁ፡ እንደልደናችሁ፡ ካባቶቻችሁ፡ ከ ተቀበላችሁት።

፲፱፤ ነገር፡ ግን፡ በከበረው፡ በበግ፡ ደም፡ ነውር፡ ርኩ ሰትም፡ የሌለበት፡ እርሱም፡ ክርስቶስ።

## ወደ፡ ዕብራውያን። ፱፤

፲፬፤ እንደት፡ ይልቁን፡ የክርስቶስ፡ ደም፡ ለዘላለ ም፡ በሚኖር፡ መንፈስ፡ ራሱን፡ ያቀረበ፡ ያለ፡ ነውር፡ ለእግዚአብሔር፡ሕሊናችሁን፡ ያነጻል፡ከሞተ፡ስራ፡ ሕያው፡ እግዚአብሔርን፡ ታገለግሉ፡ ዘንድ።

በክርስቶስ፡እምነ፡መዳን።

ወደ፡ ኤፌሶን፡ ሰዎች። ፪፡

፰፡ በጸጋው፡ ድነናችኋልና፡ በሃይማኖት። ይህም፡
ከእናንተ፡አይደለም፡የእግዚአብሔር፡ስጦታ፡ነው።
፱፡ ከምግባር፡አይደለም፡ማንም፡እንዳይመካ።

ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፭፡

፩፡ በሃይማኖትም፡ ከጸደቅን፡ ሰላም፡ አለን፡ ከእ
ግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ በጌታችን፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ።

፩፡ ዮሐንስ። ፭፡

፬፡ ከእግዚአብሔር፡ የተወለደ፡ሁሉ፡ ዓለምን፡
ያሸንፋልና። ዓለምንም፡ †የምናሸንፍበት፡ማሸነፊ፡
ሃይማኖታችን፡ ናት።

የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፳፡

፴፩፡ ይህም፡ ተጻፈ፡ታምኑ፡ ዘንድ፡ የሱስ፡እርሱ፡
ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ እንደ፡ ሆነ። ባመና
ችሁም፡ ጊዜ፡ ሕይወት፡ ይሆንላችሁ፡ዘንድ፡በስሙ።

የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፮፡

፳፰፡ አሉትም። ምን፡ እንስራ፡ የእግዚአብሔር
ን፡ ስራ፡ እናደርግ፡ ዘንድ።
፳፱፡ መለሰ፡ የሱስ፡አላቸውም። ይህ፡ ነው፡የእግ
ዚአብሔር፡ ስራ፡ ታምኑ፡ ዘንድ፡ እርሱ፡ በላከው።

# የእግዚአብሔር፡ምሕረት።

### መዝሙር። ፻፫፡

፲፩፡ ሰማይም፡ ከምድር፡ ከፍ፡ እንደ ሆነ። እንደ ሁ፡ ቸርነቱ፡ በሚፈሩት፡ ላይ፡ በረታች።

### መዝሙር። ፻፫፡

፲፯፡ የእግዚአብሔር፡ ምሕረት፡ ግን፡ በሚፈሩት፡ ላይ፡ ከዘላለም፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ዘላለም፡ ድረስ፡ ናት። ጽድቁም፡ በልጅ፡ ልጅ፡ ላይ፡ ነው።

### ሰቆቃወ፡ ኤርምያስ። ፫፡

፳፪፡ ይህ፡ የእግዚአብሔር፡ ምሕረት፡ ነው፡ ፈጽመን፡አልጠፋነምና፡ምሕረቱ፡ጸንቶ፡ስለ፡ኖረ።
፳፫፡ በጥዋት፡በጥዋት፡አዲስ፡ነውና። እውነትህ፡ ብዙ፡ነውና።

### ወደ፡ ቲቶስ። ፫፡

፭፡ ጽድቅ፡ *በማድረግ፡ ያደረግነው፡አይደለም፡ በ ምሕረቱ፡ አዳነን፡ እንጂ። †ከሁለተኛ፡ ልደቱ፡ ጥም ቀት፡ በመንፈስ፡ ቅዱስም፡ መታደስ።

### መዝሙር። ፻፲፰፡

፹፱፡ ቸርነትህ፡ ከሰማይ፡ በላይ፡ አልፎ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ነው ና፡ እውነትህም፡ እስከ፡ ደመናት፡ ድረስ፡ ነው።

እግዚአብሔር፡ ወዳ፡ እሩ፡
እንሄዳ፡ ሀንዳ፡ ያሃል።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፲፩፤

፳፰፤ ወደኔ፡ ኑ፡ እላንት፡ ደካሞች፡ ሁሉ፡ ሸክማች
ሁም፡ የከበደ፡ እኔም፡ አሳርፋችኋለሁ።

## የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፯፤

፴፯፤ ከበዓሉም፡ በ፡ታላቁ፡ በ፡ኋላኛው፡ ቀን፡ቆመ፡
የሱስ፡ ጮሆ፡ እንዲህ፡ ሲል። ማንም፡ የተጠማ፡ ቢ
ኖር፡ ወደኔ፡ ይምጣና፡ ይጠጣ።

## ትንቢት፡ ኢሳይያስ። ፩፤

፲፰፤ ኑና፡ እንተያይ፡ እግዚአብሔር፡ ይላል። ኃጢ
አታችሁ፡ እንደ፡ ቅርምዝ፡ ብትሆን፡ እንደ፡ በረደ፡ት
ነጻለች። እንደ፡ ደምም፡ ብትቀላ፡ እንደ፡ ነጭ፡ ጥጥ፡
ትጸራለች።

## የሉቃስ፡ ወንጌል። ፲፬፤

፲፯፤ ባርያውንም፡ ላከ፡ በምሳ፡ ጊዜ፡ የተጠሩትን፡
ይል፡ ዘንድ። ኑ፡ አሁን፡ ሁሉ፡ ተዘጋጅትዋልና።

## የዮሐንስ፡ ራእይ። ፳፪፤

፲፯፤ መንፈስም፡ ሙሽራዪቱም፡ ይላሉ። ና። የ
ሚሰማም፡ ይበል። ና። የተጸማም፡ ይምጣ። የወ
ደደም፡ የሕይወት፡ ውኃ፡ በከንቱ፡ ይውሰድ።

ሰዎች፡ ሁሉ፡ የእግዚአብሔር፡
ልጆች፡ አይደሉም።

## ፩፡ ዮሐንስ፡ ፫፡

፲፡ በዚህ፡ ይታወቃሉ፡ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ የ
ሰይጣንም፡ልጆች። ጽድቅ፡ የማያደርግ፡ ሁሉ፡ ከእግ
ዚአብሔር፡ አይደለም፡ ወንድሙንም፡ የማይወድ፡
እንደሁ፡ ነው።

## ወደ፡ ቆሮንቶስ፡ ሰዎች፡ ፪። ፮፡

፲፯፡ ስለዚህም፡ ከመካከላቸው፡ውጡ፡ ከርሳቸ
ውም፡ተለዩ፡እግዚአብሔር፡ይላል። ወደ፡ርኩስም፡
ሁሉ፡ አትቅረቡ፡እኔም፡እቀበላችኋለሁ።
፲፰፡ እኔም፡ አባት፡እሆናችኋለሁ፡እላንትም፡ል
ጆች፡ትሆኑልኛላችሁ። ይላል፡እግዚአብሔር፡ሁሉን፡
የሚችል።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፰፡

፲፬፡ በእግዚአብሔር፡መንፈስ፡ ተመርተው፡ የሚ
ሆኑ፡ሰዎች፡ እርሳቸው፡ የእግዚአብሔር፡ልጆች፡ ናቸ
ው።

፲፭፡ የባርነትን፡ መንፈስ፡ አልወሰዳችሁምና፡ደግ
ሞ፡ለፍርሃት፡ የልጅነትን፡መንፈስ፡ወሰዳችሁ፡ እን
ጂ፡የምትጸሩበት፡ አባ፡ አባታችን፡ ሆይ።

# እግዚአብሔር፡ ስለ፡ ጠንካራ፡
# መጠጥ፡ የተናገረው።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፲፫፡

፲፫፡ በቀኑም፡ እንሒድ፡ በቅን፡ ነገር። በዘፈንና፡
በስካር፡ አይደለም። በዝሙትም፡ አይደለም፡ በሴ
ሰኝነትም፡ በፀብም፡በቅናትም።
፲፬፡ ጌታችን፡ የሱስ፡ ክርስቶስን፡ ልበሱት፡ እንጂ።
ሥጋውንም፡ለፍትወት፡አትደግፉ።

## ትንቢት፡ ኢሳይያስ። ፭፡

፲፩፡ ወዮላቸው፡ በጥዋት፡ ለሚማልዱ፡ ስካርን፡
ለመከተል፡ በመጠጥም፡ እስከ፡ ምሽት፡ ለሚዘገ
ዩ፡ ፀጁ፡ እስኪያቃጥላቸው፡ድረስ።

## መጽሐፈ፡ ምሳሌ። ፳፫፡

፴፩፡ ወደ፡ፀጁ፡ አትመልከት፡ በቀላ፡ ጊዜ፡መልኩ
ም፡ በብርሌ፡ባንጸበረቀ፡ ጊዜ፡ኢየጸፈጠም፡ይገባል።
፴፪፡ ከጠጡት፡ በኋላ፡እንደባብ፡ይነድፋልና፡እን
ደ፡ ጉበናም፡ መርዙን፡ያፈሳል።

## የሉቃስ፡ ወንጌል። ፳፩፡

፴፬፡ በነፍሳችሁ፡ግን፡ተጠንቀቁ፡ ልባችሁ፡ በሥሥ
ት፡ በስካርም፡ እንዳይዝነን፡ ስለ፡ አደርም፡ በማሰ
ብ። ያቺም፡ ቀን፡ ድንገት፡ እንዳይደርስባችሁ።

ቃዐም፡ ነግረኛነት፡ ለይበቃም።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፳፪፥

፴፯፥ የሱስም፡አለው። እግዚአብሔርን፡አምላክ ህን፡ ትወድ፡ ዘንድ፡ ከፍጹም፡ ልብህ፡ ከፍጹምመ፡ ነፍስህ፡ ከፍጹምም፡ አሳብህ።

፴፰፡ ይህች፡ መጀመርያዪቱ፡ ትእዛዝ፡ የምትበል ጠው፡ ናት።

## ወዮ፡ ዕብራውያን። ፲፥

፳፭፡ እርሱ፡በርሳችሁ፡ራሳችሁን፡ ተመካከሩ፡ እን ጂ፡ ዛሬ፡ በሚባልበቱ፡ ቀን፡ ሁሉ፡ ከላንት፡ ማንም፡ በኃጢአት፡ ስሕተት፡ እንደይደኦና።

## መጽሐፈ፡ ምሳሌ። ፲፬፥

፲፪፥ ለሰው፡ቅን፡የምትመስል፡ መንገድ፡ አለች። ፍጻሜዋ፡ግን፡የሞት፡መንገድ፡ናት።

## ወ፩፡ ጢሞቴዎስ፡ ፩። ፩፡

፲፫፡ እኔም፡እመሰግነዋለሁ፡ ክርስቶስ፡ የሱስ፡ጌታ ችንን፡ ያበረታኝ፡ የታመነም፡ የቈጠረኝ፡ ለመልእ ክቱም፡ የሠራኝ።

፲፬፡ እኔን፡ቀድሞ፡ ተሳዳቢ፡የነበርሁትን፡ አሳዳጅ ም፡የማንንም፡ነገርም፡ያደረግሁ። ነገር፡ግን፡ይቅር፡ተ ባልሁ፡ይህን፡ባለማመን፡አደርግ፡ነበርሁና፡ባላውቅ፡

# አትታለሉ ።

ያዕቆብ። ፩፥

፳፪፥ ቃልንም፡ አድራጊዎች፡ ሁኑ፡ ሰሞችም፡ ብቻ፡ አይደለውም፡ ራሳችሁን፡ እንደታሉ።

ወደ፡ ቆርንቶስ፡ ሰዎች፡ ፩። ፮፥

፱፥ ወይስ፡ አታውቁምን፡ ግፈኞች፡ የእግዚአብሔ
ርን፡ መንግሥት፡ እንደይወርሱ። አትሳቱ። ዘማዊ፡ሰ
ዎች፡ጣዖትም፡ የሚያመልኩ፡አመንዝሮችም፡ ቀላ
ጮችም፡ከወንድ፡ጋራ፡የሚተኙም።
፲፥ ሌቦችም፡ ሰስታሞችም፡ ሰካሮችም፡ ተሳደቦች
ም፡ ነጣቆችም፡ የእግዚአብሔርን፡ መንግሥት፡ አይ
ወርሰዋትም።

ወደ፡ ኤፌሶን፡ ሰዎች። ፭፥

፮፥ ማንም፡ አያታላችሁ፡ በምንም፡ ነገር፡ በዚህ፡
ነገር፡ምክንያት፡የእግዚአብሔር፡ ቍጣ፡ ይመጣልና፡
በማይታዘዙ፡ ልጆች፡ ላይ።

፩፡ ዮሐንስ፡ ፫፥

፯፥ ልጆቼ፡ ሆይ፡ ማንም፡ አያስታችሁ። ጽድቅ፡ የ
ሚያደርግ፡ ጻድቅ፡ነው፡ ያም፡ ጻድቅ፡ እንደ፡ ሆነ።
፰፥ ኃጢአትም ፡ የሚያደርግ፡ እርሱ፡ ከሰይጣን፡
ነው፡ ሰይጣን፡ ከጥንት፡ ኃጢአትን፡ አድርጓልና።

# ሐጢአት፡ ሞትን፡ ያመጣል።

### ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፭፡

፲፪፡ ስለዚህም፡ ኃጢአት፡ ወደ፡ ዓለም፡ እንደ፡ ገባች፡ ባንድ፡ ሰው፡ ምክንያት፡ በኃጢአትም፡ ሞት፡ ገባ። እንዲሁም፡ ሞት፡ አለፈ፡በሰው፡ሁሉ፡ላይ፡ሁሉ፡ በድለዋልና።

### ያዕቆብ። ፩፡

፲፭፡ መመኘት፡ ግን፡ ባረገዘች፡ ጊዜ፡ ኃጢአትን፡ ትወልደለች። ኃጢአትም፡ በተፈጸመች፡ ጊዜ፡ ሞት፡ ትወልደለች።

### ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፰፡

፮፡ የሥጋ፡አሳብ፡ ሞት፡ነውና። የመንፈስ፡አሳብ፡ ግን፡ ሕይወትና፡ ሰላም፡ ነው።

### ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፮፡

፳፩፡ ነገር፡ግን፡ምን፡ፍሬ፡ ነበራችሁ፡ የዚያን፡ጊዜ፡ በስራችሁ፡ዛሬ፡ ከርሱ፡ የምታፍሩበት። የዚያ፡ስራ፡ ፍጻሜ፡ ሞት፡ነውና።

### መጽሐፈ፡ ምሳሌ። ፲፩፡

፲፱፡ ጽድቅ፡ ወደ፡ ሕይወት፡ ይመራል። ክፋትን፡ የሚከተል፡ ግን፡ ሞት፡ ያዘጋጀል።

ክርስቶስ፡ ሞትን፡ አሸነፈ ።

የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፩፡

፵፫፡ ይህንንም፡ባለ፡ጊዜ፡በታላቅ፡ ቃል፡ጮኸ። አል
ዓዛር፡ ና፡ወደ፡ ሜዳ፡ ውጣ።
፵፬፡ የሞተውም፡ወጣ፡እጆቹ፡እግሮቹም፡ በከፈ
ን፡ ተጠቅልለው። ፊቱም ፡ ተጠቅሎ፡ በመጠምጠ
ሚያ።አላቸው፡ የሱስ ። ፈቱት፡ ተውትም፡ ይሒድ።

የዮሐንስ፡ ራእይ። ፩፡

፲፰፡ ሕያውም፡ ሙቼም፡ ነበርሁ። እነሆም፡ ሕያ
ው፡ ነኝ፡ ለዘላለሙ። አሜን። የሲኦልና፡ የሞት፡ መ
ክፈቻም፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ነው።

የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፡

፲፯፡ ስለዚህ፡አብ፡ ይወደኛል፡እኔ፡ ነፍሴን፡ አሰጣ
ለሁና፡ ደግሞ፡ እወስዳት፡ ዘንድ።
፲፰፡ ማንም፡ከኔ፡አይወስዳትም፡ ነገር፡ግን፡ እኔ፡ በ
ፈቃዴ፡አሰጣታለሁ።ለኔ፡ችሎት፡ አለኝ፡ አሰጣት፡ ዘ
ንድ፡ደግሞም፡ችሎት፡ አለኝ፡ እወስዳት፡ ዘንድ። ይ
ህንን፡ትእዛዝ፡ካባቴ፡ ተቀበልሁ።

የሉቃስ፡ ወንጌል። ፯፡

፲፬፡ ቀርቦም፡ቃሬዛውን፡ነካ፡ የተሸከሙትም፡ ቆ
ሙ። አለም። አንተ፡ ጐበዝ፡ እልሃለሁ፡ ተነሣ።
፲፭፡ የሞተውም፡ተቀመጠ፡ይጫወትም፡ጀመረ።

# አሥሩ ፡ ትእዛዛት ።

## ኦሪት፡ ዘዳግም። ፭፡

፯፡ ሌሎች፡ አማልክት፡ በፊቴ፡ አይሁኑልኝ።

፰፡ የተወቀረውን፡ የተጸረበውንም፡ ሥእልና፡ም
ሳሌን፡ ሁሉ፡ አታድርግ፡ በላይ፡ በሰማይ፡ ካለው።
በታች፡ በምድርም፡ ካለው፡ በውኃ፡ ካለውም፡ በም
ድር፡ ታች።

፱፡ አትስገድላቸው፡ አታምልካቸውም። እኔ፡ እ
ግዚአብሔር፡ አምላክኽ፡ ቅናተኛ፡ አምላክ፡ ነኝና፡
ያባቶችን፡ ኃጢአት፡ በልጆች፡ ላይ፡ የምመልሰው፡ እ
ስከ፡ ሦስት፡ እስካራትም፡ ትውልድ፡ ድረስ፡ በሚጸ
ሉኝ።

፲፡ ምሕረትም፡ የማደርግ፡ ለብዙ፡ ሺህ፡ ለሚወ
ዱኝ፡ ትእዛዜንም፡ ለሚጠብቁ።

፲፩፡ የእግዚአብሔርን፡ ያምላክኽን፡ ስም፡ በነገር
ኽ፡ ከንቱ፡ አታድርገው። እግዚአብሔር፡ ስሙን፡ ከ
ንቱ፡ የሚያደርገውን፡ ሳይቀሥፈው፡ አይተወው
ምና።

፲፪፡ የሰንበትን፡ ቀን፡ ጠብቅ፡ ትቀድሰው፡ ዘንድ፡
እግዚአብሔር፡ አምላክኽ፡ እንደዘዘኽ።

፲፫፡ ስድስት፡ ቀን፡ስራ፡ ስራኽንም፡ሁሉ፡አድርግ።

፲፬፡ ሰባተኛውም፡ ቀን፡ የሰንበት፡ ቀን፡ ነው፡ ለእ
ግዚአብሔር፡ ላምላክኽ። ስራን፡ ሁሉ፡ አትስራበት፡

አንተ፡ ወንድ፡ ልጅኽም፡ ሴት፡ ልጅኽም፡ ሎሌኽ
ና፡ ገረድኽ፡ በሬኽም፡ አህያኽም፡ ከብትኽም፡ ሁ
ሉ፡ በደጅኽም፡ ውሥጥ፡ ያለ፡ መጻተኛ። ሎሌኽና፡
ገረድኽ፡ ያርፉ፡ ዘንድ፡ አንተ፡ እንድታርፍ።
፲፭፡ አንተም፡ በምስር፡ ባርያ፡ እንደ፡ ነበርኽ፡ አስ
ብ፡ እግዚአብሔርም፡ አምላክኽ፡ ከዚያ፡ አወጣ
ኽ፡ በጸናች፡ እጅ፡ ከፍ፡ ባለችም፡ ክንድ። ስለዚኽ፡
እግዚአብሔር፡ አምላክኽ፡ የሰንበትን፡ ቀን፡ ትጠ
ብቅ፡ ዘንድ፡ አዘዘኽ።
፲፮፡ አባትኽንና፡ እናትኽን፡ አክብር፡ እግዚአብ
ሔር፡ አምላክኽ፡ እንዳዘዘኽ። ዘመንኽ፡ እንዲረ
ዝም፡ መልካምም፡ እንዲሆንልኽ፡ እግዚአብሔር፡
አምላክኽ፡ በሚሰጥኽ፡ ምድር።
፲፯፡ አትግደል።
፲፰፡ አታመንዝር።
፲፱፡ አትስረቅ።
፳፡ በባልንጀራኽም፡ በሐሰት፡ አትመስክር።
፳፩፡ የባልንጀራኽንም፡ ምሽት፡ አትመኝ፡ የባል
ንጀራኽንም፡ ቤት፡ አትመኝ። እርሻውንም፡ ሎሌ
ውንም፡ ገረዲንም፡ በሬውንም፡ አህያውንም፡ ለባ
ልንጀራኽም፡ የሚሆነውን፡ ነገር፡ ሁሉ።

የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፫፡

፴፬፡ አዲስ፡ትእዛዝ፡እሰጣችኋለሁ፡እርሱ፡በርሳ
ችሁ፡ ትዋደዱ፡ ዘንድ። እንደ፡ ወደድኋችሁ፡ እላንተ
ም፡ ደግሞ፡ እርሱ፡በርሳችሁ፡ ትዋደዱ፡ ዘንድ።

# ከእግዚአብሔር፡መሸሸግ፡
# አይቻልም ።

## መጽሐፈ፡ ምሳሌ። ፲፭፡

፫፡ የእግዚአብሔር፡ ዓይኖች፡ በስፍራው፡ ሁሉ፡ ና
ቸው። ጻድቃንንና፡ ኃጢአተኞችን፡ ይመለከታሉ።

## መዝሙር። ፻፴፱፡

፰፡ ወደ፡ ሰማይ፡ብወጣ፡ አንተ፡ከዚያ። ነህ። ም
ንጣፌንም፡ በሢኦል፡ ባነጥፍ፡ ከዚያም፡ እነሆ፡ አን
ተ፡ አለኸ።
፲፪፡ ባንተ፡ ዘንድ፡ ጨለማ፡ አይጨልምምና፡ ሌሊ
ቱም፡ እንደ፡ ቀን፡ ያበራል። እንደ፡ጨለማው፡እንደ
ሁ፡ ብርሃን፡ ነው።

## መጽሐፈ፡ ኢዮብ። ፴፬፡

፳፩፡ ዓይኖቹ፡ በሰው፡ መንገድ፡ ላይ፡ ናቸውና፡ እር
ምጃቸውንም፡ ሁሉ፡ ያያል።
፳፪፡ ጨለማና፡ የሞት፡ ጥላም፡ ኃጢአት፡የሚሰሩ
ት፡ ይሰወሩባቸው፡ ዘንድ፡ የለም።

## ትንቢተ፡ ኤርምያስ። ፳፫፡

፳፬፡ ሰው፡ በሥውር፡ ቢሸሸግ፡ እኔ፡ አላየውምን፡
ይላል፡ እግዚአብሔር። በሰማይና፡ በምድር፡ የመላ
ሁ፡ አይደለሁምን፡ ይላል፡ እግዚአብሔር።

# የኃጢአተኞች፡ የዘላለም፡ ቅጣት ፡፡

### የማቴዎስ፡ ወንጌል፡፡ ፲፫፡

፵፩፡ የሰው፡ ልጅ፡ መልክተኞቹን፡ ይልካል፡ ከመ
ንግሥቱም፡ እንቅፋትን፡ ሁሉ፡ ይሰበስባሉ፡ ዓመፃ
ም፡ የሚያደርጉን፡፡
፵፪፡ ወደ፡ እቶነ፡ እሳትም፡ ይጥለዋቸዋል፡ ልቅሶ፡
ጥርስ፡ ማፋጨትም፡ ወደለበት፡፡

### መዝሙር፡፡ ፱፡

፲፯፡ ረሲዓን፡ወደ፡ሲኦል፡ይመለሳሉ፡፡ እግዚአብ
ሔርንም፡የሚረሱ፡አሕዛብ፡ሁሉ፡፡

### ፪፡ ጴጥሮስ፡ ፫፡

፯፡ ዛሬም፡ የሚሆኑ፡ ሰማያት፡ ምድር፡ በዚኹ፡ ቃ
ል፡ጸንተዋል፡ለሳት፡ ተጠብቀው፡እስከ፡ ፍርድ፡ ቀን፡
እስከ፡ ኃጢአተኞችም፡ጥፋት፡ ቀን፡፡

### የዮሐንስ፡ ራእይ፡፡ ፳፡

፲፭፡ ማንም፡ በሕይወት፡ መጽሐፍ፡ ተጽፎ፡ ባይገ
ኝ፡ በእሳት፡ ባሕር፡ ተጣለ፡፡

### የማቴዎስ፡ ወንጌል፡፡ ፳፭፡

፵፮፡ እለዚያም፡ወደ፡ዘላለም፡ሥቃይ፡ይሔዳሉ፡፡
ጻድቃን፡ ግን፡ ወደ፡ ዘላለም፡ ሕይወት፡፡

## የወጻሬት፡ ዓጃንት ።

### ፪፡ ጴጥሮስ፡ ፪፡

፱፡ እግዚአብሔር፡ ያውቃል፡ የሚያምልኩትን፡
ከመከራ፡ያድን፡ዘንድ፡ ኃጢአተኞችን፡ግን፡ለፍርድ፡
ቀን፡ሊሣቀዩ፡ይጠብቃቸዋል።

### የሐዋርያት፡ ሥራ። ፲፯፡

፴፩፡ በዓለሙ፡የሚፈርድበትን፡ቀን፡ አቁሞዋል
ና፡ በቅን፡ ፍርድ፡ በዚያ፡ ሰው፡ እጅ፡ በመረጠው። ስ
ለዚህም፡ የታመነ፡ ምስክር፡ለሁሉ፡ሰጠው፡እርሱን፡
በማስነሣቱ፡ ከሙታን።

### ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፲፬፡

፲፪፡ አሁንም፡ ከኛ፡ *ኢያንዳንዳችን፡ የእግዚአብ
ሔር፡ ምላሽ፡ ይሰጣል።

### ወደ፡ ዕብራውያን። ፱፡

፳፯፡ በሰዎችም፡ ላይ፡ እንደ፡ ተሠራ፡ *እንደግዜ፡
ይሞቱ፡ ዘንድ፡ ከሞቱ፡ በኋላም፡ ፍርድ፡ እንደለባቸ
ው፡

### ፩፡ ዮሐንስ። ፬፡

፲፯፡ በዚህ፡ ፍቅሩ፡ ከኛ፡ ጋራ፡ ተፈጸመች፡ ድፍረ
ት፡ ትሆንልን፡ዘንድ፡በፍርድ፡ቀን። እርሱ፡እንደሆነ፡
እንዲሁም፡ እኛ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ነነ።

# የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ፀጋ ።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፭፡

፲፭፡ ነገር፡ግን፡ጸጋው፡ እንደ፡ኃጢአቱ፡መጠን፡አይ
ደለም፡ ባንድ፡ ሰው፡ ኃጢአት፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ሙተ
ዋልና። እጅግም፡ ደግሞ፡ የእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡ ስጦ
ወታውም፡ ባንድ፡ ሰው፡ ጸጋ፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እ
ጅግ፡ ትበዛለች፡ በብዙ፡ ሰዎች፡ ላይ።

## የሐዋርያት፡ ስራ። ፬፡

፴፫፡ ሐዋርያትም፡ በየሱስ፡ በጌታ፡ትንሣኤ፡ምስ
ክርነት፡ ይገልጡ፡ ነበሩ፡ በታላቅ፡ኃይል። ታላቅም፡ ጸ
ጋ፡ በሁሉ፡ ላይ፡ ነበረባቸው።

## ወደ፡ ቆሮንቶስ፡ ሰዎች፡ ፪። ፱፡

፲፭፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁነው፡ስለማ
ይነገረው፡ ጸጋው።

## ወደ፡ ቆሮንቶስ፡ ሰዎች፡ ፰። ፱፡

፱፡ የጌታችንን፡ የየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ጸጋ፡ አውቃች
ኋልና። ስለእናንተ፡ ድኻ፡ ሆነዋልና፡ ባለጠጋ፡ ሳለ። እ
ናንተ፡ በድህነቱ፡ ባለጠጎች፡ ትሆኑ፡ ዘንድ።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፱፡

፲፮፡ አሁንም፡ ይህ፡ ለወደደ፡ ለሮጠም፡ አይደለ
ም። እግዚአብሔር፡ ይቅር፡ ላለው፡ ነው፡ እንጂ።

ንስሐ ።

## የሐዋርያት፡ ስራ። ፫፡

፲፱፡ አሁንም፡ ንስሐ፡ ግቡ፡ ተመለሱም፡ ኃጢአታ
ችሁ፡እንድጠፋላችሁ፡ የዕረፍትም፡ዘመን፡ ትመጣ
ላችሁ፡ዘንድ፡ከእግዚአብሔር፡ፊት።

## የሉቃስ፡ ወንጌል። ፲፫፡

፫፡ እላችኋለሁ፡አይደለም።ነገር፡ግን፡ንስሐ፡ ባት
ገቡ፡ሁላችሁ፡እንደሁ፡ትጠፋላችሁ።

## የሐዋርያት፡ ስራ። ፪፡

፴፰፡ ጴጥሮስም፡ አላቸው። ንስሐ፡ ግቡ፡ ከላንት
ም፡ ሁሉ፡ ኢያንዳንዳችሁ፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡
ይጠመቅ፡ኃጢአት፡ ለማስተስረይ። የመንፈስ፡ቅዱ
ስንም፡ ጸጋ፡ ትወስዷላችሁ።

## የሉቃስ፡ ወንጌል። ፲፭፡

፯፡ እላችኋለሁ። እንዲሁ፡ ደስታ፡በሰማይ፡እንዲ
ሆን፡ ንስሐ፡ በሚገባ፡ባንድ፡ኃጢአተኛ፡ከዘጠና፡ዘጠ
ኝ፡ ጻድቃን፡ ይልቅ፡ ንስሐ፡ የማይሹ።

## የሐዋርያት፡ ስራ። ፲፯፡

፴፡ ያነንም፡ የድንቁርናውን፡ ወራት፡ እግዚአብ
ሔር፡ አሳለፈው። አሁን፡ ግን፡ሰውን፡ ሁሉ፡በየቦታቸ
ው፡ አዘዘ፡ ንስሐ፡ ይገቡ፡ ዘንድ።

# የኃጢአት፡ ይቅርታ።

## ትንቢተ፡ ኢሳይያስ። ፶፭፡

፯፤ በደለኛ፡ መንገዱን፡ ይተው፡ ክፉ፡ሰውም፡አሳ
ቡን። ወደ፡ እግዚአብሔርም፡ ይመለስ፡  መረውማ
ል፡ወደምላካችንም፡ይቅርታው፡ብዙ ነውና።

## የሐዋርያት፡ ሥራ። ፭፤

፴፩፡ ይህን፡እግዚአብሔር፡በቀኙ፡ አስቀመጠ
ው፡ራስ፡መድኃኒትም፡አድርጎ፡ለእሥራኤል፡ንስሐ፡
ይሰጥ፡ ዘንድ፡የኃጢአትም፡ ስርየት።

## የዮሐንስ፡ ራእይ። ፫፤

፳፤ እነሆ፡እኔ፡ በደጅ፡ ቁሚያለሁ፡ ደጅም፡ አመ
ታለሁ። ማንም፡ድምጼን፡ ቢከፍትልኝም፡ ወደርሱ፡
እገባለሁ። ከርሱም፡ ጋራ፡ እራቴን፡ እበላለሁ፡ እር
ሱም፡ከኔ፡ጋራ።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፮፤

፲፬፡ ለሰዎች፡ ኃጢአታቸውን፡ ይቅር፡ ብትሉ፡ የሰ
ማዩ፡አባታችሁ፡ ደግሞ፡ ይቅር፡ ይላችኋልና።

## ትንቢተ፡ ሕዝቅኤል። ፲፰፡

፳፩፡ ኃጢአተኛም፡ ካደረጋት፡ኃጢአት፡ ሁሉ፡ንስ
ሐ፡ ቢገባ፡ ትእዛዜንም፡ ሁሉ፡ ቢጠብቅ፡ ፍርድም፡
ጽድቅም፡ ቢሠራ፡ በደህንነት፡ ይኖራል፡ አይሞትም።

# ከዓለማዊ፡ ተግባር፡ መለየት ።

## ፩፡ ዮሐንስ፡ ፪፡

፲፭፡ ዓለምን፡አትውደዱ፡በዓለምም፡ያለውን። ዓለምን፡ በሚወድ፡ ሰው፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ የለበትም።

፲፮፡ በዓለም፡ያለው፡ሁሉ፡ የሥጋ፡ መመኘት፡የዓይንም፡ መመኘት፡ የሰውም፡ ትምክሕት። ይህም፡ ከአብ፡ አይደለም፡ ከዓለም፡እንጂ።

## ትንቢት፡ ኢሳይያስ። ፩፡

፲፮፡ ታፀቡ፡ሰውነታችሁንም፡አንጹ። የስራችሁን፡ ክፋት፡ባይኔ፡ ፊት ፡ አስወግዱ። ክፋ፡ ማድረግን፡ ተው።

## ወደ፡ ቆላስይስ፡ ሰዎች፡ ፫፡

፪፡ በላይ፡ያለችውን፡ አስቡ፡ በምድርም፡ ያለችውን፡ አይደለም።

## ያዕቆብ። ፬፡

፬፡ እላንት፡ አመንዝሮች፡ አመንዝራይቶችም፡ አታውቁምን፡ የዓለም፡ፍቅር፡ በእግዚአብሔር፡ ላይ፡ ጸላትነት፡ እንደ፡ ሆነች። የዓለም፡ ወዳጅ፡ ሊሆን፡ የሚወድ፡ የእግዚአብሔር፡ ጸላት፡ ሁኖ፡ ተገኘ።

ክፍል፡ ሰባት ።

## የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፫፤

፫፡ የሱስም፡ መለሰ፡ አለውም። እውነት፡ እልሃለ
ሁ። ሰውም፡ከላይ፡ ካልተወለደ፡ የእግዚአብሔርን፡
መንግሥት፡ያይ፡ ዘንድ፡ አይችልም።

## ወደ፡ ቆሮንቶስ፡ ሰዎች፡ ፪፤ ፭፡

፲፯፡ ብክርስቶስም፡ የሆነው፡ ሁሉ፡ እርሱ፡ አዲስ፡
ፍጥረት፡ነው። ተአሮጌው፡ ስራ፡ ፈጽሞ፡ሔደ፡ እነሆ፡
ሁሉ፡ ታደሰ።

## ፩፤ ዮሐንስ። ፭፡

፲፰፡ እናውቃለን፡ ከእግዚአብሔር፡ የተወለደ፡
ሁሉ፡ ኃጢአት፡ እንደይሰራ፡ከእግዚአብሔር፡የተወ
ለደ፡ ራሱን፡ ይጠብቃል፡ እንጂ፡ ክፉም፡ አይነካው
ም።

## ፩፤ ጴጥሮስ። ፩፤

፳፫፤ ከሚጠፋ፡ ዘር፡ አልተወለደችሁምና፡ ነገር፡
ግን፡ከማይጠፋ፡ ከዘላለሙ፡ ከሕያው፡ከእግዚአብ
ሔር፡ ቃል፡ የተነሣ።

## ፩፤. ዮሐንስ፡ ፪፤

፳፱፡ ጻድቅ፡ እንደሆነ፡ ካወቃችሁ፡ እወቁ፡ ጽድ
ቅ፡ የሚሰራ፡ ሁሉ፡ ከርሱ፡ የተወለደ፡ እንደሆነ።

## በኃጢአት፡ሞት፡
## በክርስቶስ፡ትንሣኤ።

### ወደ፡ ኤፌሶን፡ ሰዎች። ፪፡

፩፡ እላንትንም፡ፈጽሞ፡አደናችሁ፡ሙታን፡ስትሆ
ኑ፡በመተላለፋችሁና፡በኃጢአታችሁ።
፮፡ ከርሱም፡ጋራ፡አስነሣ፥ከርሱም፡ጋራ፡በሰማያ
ት፡ አስቀመጠ፥ በክርስቶስ፡ የሱስ።

### ወደ፡ ቆላሳይስ፡ ሰዎች፡ ፫፡

፩፡ እንግዲህ፡ ከክርስቶስ፡ ጋራ፡ *የተነሣችሁ፡ እን
ደ፡ሆናችሁ፡ በላይ፡ ያለውን፡እሹ፡ ክርስቶስ፡ በእግዚ
አብሔር፡ቀኝ፡ ተቀምጦ፡ ወደለበቱ።

### ፩፡ ጴጥሮስ። ፪፡

፳፬፡ እርሱ፡  ኃጢአታችነን፡ በሥጋው፡ በንጨት፡
ላይ። ከኃጢአት፡ ወጥተን፡ለጽድቅ፡እንኖር፡ዘንድ።
በቍስሉ፡ የተፈወሳችሁ።

### ወደ፡ ገላትያ፡ ሰዎች። ፭፡

፳፬፡ የክርስቶስ፡ ወገኖችም፡ ሥጋቸውን፡ ፈቃዎ
ው፡ሰቀሉ፡ከሕማማትና፡ ከመመኘት፡ጋራ።

# የዘላዓለም፡ ሕይወት ።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፮፡

፳፫፡ የኃጢአት፡ዋጋ፡ ሞት፡ነውና፡የእግዚአብሔር፡ጸጋ፡ግን፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ ነው፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡በጌታችን።

## የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፫፡

፴፮፡ በልጁ፡ ያመነ፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ አለው። ልጁንም፡ የማይሰማ፡ሕይወትን፡ አያይም። የእግዚአብሔር፡ ቍጣ፡ በላዩ፡ ይኖራል፡ እንጂ።

## ወደ፡ ገላትያ፡ ሰዎች። ፮፡

፰፡ ለሥጋው፡የዘራ፡ ከሥጋው፡ ጥፋትን፡ያጭዳል፡ ለመንፈስም፡ የዘራ፡ ከመንፈስ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት፡ ያጭዳል።

## የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፭፡

፳፬፡ እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ። ነገሬን፡ የሚሰማ፡ በሰደደኝም፡ የሚያምን፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ አለው፡ ወደ፡ ፍርድም፡ አይመጣም፡ከሞት፡ ወደ፡ ሕይወት፡ ተሻገረ፡ እንጂ።

# የመዳን፡ማረጋገጫ።

### ወደ፡ ገላትያ፡ ሰዎች። ፬፥

፮፥ ልጆችም፡ በሆናችሁ፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ የልጁን፡ መንፈስ፡ በልባችሁ፡ ላከ፡ እንዲህ፡ የሚጸራ፡ አባታችን፡ አብ።

### ፩፡ ዮሐንስ። ፫፥

፲፰፥ ልጆቼ፡ ሆይ፡ እንውደድ፡ በቃል፡ በመላስም፡
በስራና፡በውነት፡እንጂ። ያዕ፡ ፩፡ ፳፪፡፡ ፫፡ ፪፥ ፲፫፡፡
፲፱፥ በዚህም፡ እናውቃለን፡ እኛ፡ ከውነት፡ እንደ
ሆነ፡ በፊቱም፡ ልባችነን፡ እናሳርፋለን።

### ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፰፡

፲፯፥ ያም፡ መንፈስ፡ለመንፈሳችን፡ ይመሰክራል፡ እኛ፡የእግዚአብሔር፡ልጆች፡እንደ፡ሆነ።

### የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፫፥

፳፩፥ ይህነንም፡ብሎ፡የሱስ፡በመንፈስ፡ታወከ፡መሰከረም፡አለም። እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ። አንዱ፡ከእናንተ፡አሳልፎ፡እንዲሰጠኝ።

### ፩፡ ዮሐንስ። ፬፥

፲፫፥ በዚህ፡ እናውቃለን፡ እኛ፡ በርሱ፡ እንድንኖር፡ እርሱም፡ በኛ፡ ከመንፈሱ፡ ሰጥቶናልና።

ክርስቶስ፡በወስጣችን፡ሊፀፅር፡
የሚ/ነጠን፡ጻስታ።

## የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፡

፲፡ ዛሬም፡ወደኝት፡ እመጣለሁ። ደህንነም፡ በሙ
ላም፡እንገራለሁ፡ደስታና፡በርካታም፡እንደ፡ሊያዝም።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፲፬፡

፲፯፡ የእግዚአብሔር፡ መንግሥት፡ መብል፡ መጠ
ጥም፡አይደለምና። ነገር፡ግን፡ጽድቅ፡ነው፡ሰላምም፡
ደስታም፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ።

## መዝሙር። ፲፮፡

፲፩፡ የሕይወትን፡ መንገድ፡ታስታውቀኛለህ። በ
ፊትህ፡ የደስታ፡ ጽጋብ፡ነው፡ ሥምረትም፡ በቀኝህ፡
ለዘላለም።

## ወደ፡ ገላትያ፡ ሰዎች። ፪፡

፳፡ ከክርስቶስ፡ ጋራ፡ ተሰቀልሁ። ሕያው፡ ነኝ፡ እኔ
ም፡ አይደለሁም፡ ክርስቶስ፡ በኔ፡ ሕያው፡ ነው፡ እን
ጂ። ይህችም፡ ሕይወት፡ ዛሬ፡ እኔ፡ ያለሁባት፡ በሥ
ጋ፡ የሃይማኖት፡ ሕይወት፡ ናት፡ በእግዚአብሔር፡ ል
ጅ፡ በወደደኝ፡ ራሱንም፡ ስለኔ፡ በለወጠ።

# ለጌታችን፡መታዘዝ፡ አስፈላጊነት።

## በመጽሐፈ፡ ሳሙኤል፡ ቀዳማዊ። ፲፪፡

፲፭፡ እላንተ፡ ግን፡ የእግዚአብሔርን፡ነገር፡ ባትሰ
ሙ፡ ነገሩ፡ንም፡ ባትቀበሉሙ፡የእግዚአብሔር፡እጅ፡
በላያችሁ፡ትሆናለች፡ ባባቶቻችሁ፡ላይ፡እንደ፡ሆነች።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፮፡

፲፮፡ ወይስ፡አታውቁምን፡ ሰውነታችሁን፡ ለምታ
ዘጋጁለት፡ለርሱ፡ባሮች፡ እንድትሆኑ፡ ልትሰሙት፡ እ
ላንት፡ለርሱ፡ ባሮች፡ እንደ፡ ሆናችሁ፡ ለምትታዘዙለ
ት።ለኃጢአትም፡ቢሆን፡ለሞት፡ለመታዘዝም፡ ቢሆ
ን፡ለጽድቅ።

## ወደ፡ ተሰሎንቄ፡ ሰዎች፡ ፪። ፩፡

፯፡ ለላንትም፡ዛሬ፡ጭንቀት፡ ለምታዩት፡ዕረፍት፡
ይሰጣችኋል፡ከኛ፡ጋራ፡ የሱስ፡ጌታ፡ ከሰማይ፡ በተገለ
ጠ፡ጊዜ፡ከኃይሉ፡ መላእክት፡ጋራ።
፰፡ በሚቃጠል፡እሳት፡ ተበቅሎ፡አምላክን፡ ከማ
ያውቁ፡ለጌታችንም፡ ለየሱስ፡ ክርስተስ፡ ወንጌል፡ ከ
ማይታዘዙ።
፱፡ እለዚህም፡የዘላለም፡ ጥፋትን፡ ፍርድ፡ ይወስ
ዷሉ፡ከጌታ፡ፊት፡ከኃይሉም፡ክብር።

# ስለክርስቶስ፡መመስከር፡ አስፈላጊነት።

### ፩፡ ዮሐንስ፡ ፪፡

፳፫፡ ወልድን፡ የሚክድ፡ ሁሉ፡ አብ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ የለም። በወልድ፡ የሚያምን፡ አብም፡ ደግሞ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ነው።

### የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፲፡

፴፪፡ በኔም፡ የሚያምንብኝ፡ ሁሉ፡ በሰው፡ ፊት፡ እኔም፡ ደግሞ፡አምንበታለሁ፡ በሰማያት፡ ባለው፡ ባባቴ፡ ፊት።

፴፫፡ በሰው፡ፊትም፡የካደኝን፡እኔም፡ደግሞ፡በሰማያት፡ባለው፡ ባባቴ፡ ፊት፡ እክደዋለሁ።

### ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፲፡

፱፡ ባፍህ፡ብትነግር፡የሱስ፡ጌታ፡እንደ፡ሆነ፡በልብህም፡ ብታምን፡ እግዚአብሔር፡ ከሙታን፡ እንዳስነሣው፡ ትድናለህ።

፲፡ ሰው፡በልቡ፡ያምናልና፡ለጽድቅ፡ ዘንድ። በአፉም፡ ያስታውቃል፡ ይድን፡ ዘንድ።

### ወደ፡ ፊልጵስዩስ፡ ሰዎች። ፪፡

፲፩፡ መላስም፡ ሁሉ፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ጌታ፡ እንደ፡ ሆነ፡ያስታውቅ፡ዘንድ፡ለእግዚአብሔር፡አብ፡ ክብር።

ሰይጣን፡ ተቃዋሚ፡ ጠላታችን።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፬፡

፩፡ ከዚያ፡ወዲያ፡ መንፈስ፡የሱስን፡ወደ፡ ምድረ፡
በዳ፡ አወጣው፡ ከዲያብሎስ፡ሊፈተን።
፲፡ የዚያን፡ጊዜ፡ የሱስ፡ አለው። ከኔ፡ ራቅ፡ አንተ፡
ሰይጣን። ተጽፏልና፡ ለእግዚአብሔር፡ለአምላክ
ህ፡ ስገድ፡ እርሱንም፡ ብቻውን፡ አምልክ።
፲፩፡ ከዚያ፡ ወዲያ፡ ሰይጣን፡ ተወው፡ መላእክት
ም፡ እነሆ፡ መጡ፡ ለርሱም፡ ያገለግሉ፡ ነበሩ።

## የሐዋርያት፡ ሥራ። ፳፮፡

፲፰፡ ዓይኖቻቸውን፡ ትከፍት፡ ዘንድ፡ ከጨለማ፡ ወ
ደ፡ብርሃን፡ እንዲመለሱ። ለሰይጣንም፡ ከመግዛት፡
ወደ፡እግዚአብሔር። የኃጢአታቸውን፡ ስርየት፡ይወ
ስዱ፡ዘንድ፡ ርስትም፡ ከቅዱሳን፡ ጋራ፡ በኔ፡በማመና
ቸው።

## ወደ፡ ተሰሎንቄ፡ ሰዎች፡ ፪። ፪፡

፱፡ የዚያ፡ መምጣቱ፡ በሰይጣን፡ ሥራ፡ ነው፡ በኃይ
ል፡ ሁሉ፡ በምልክትም፡ ባሰትም፡ ተአምራት።

## ወደ፡ ኤፌሶን፡ ሰዎች። ፮፡

፲፩፡ የእግዚአብሔርን፡እቃ፡ጦር፡ሁሉ፡ልበሱ፡ የሰ
ይጣንን፡ተንኰል፡ትቋቋሙ፡ዘንድ፡እንዲቻላችሁ።

በሰይጣን ላይ ጥቅስ ።

## ያዕቆብ። ፬፥

፯፥ አሁንም፡ለእግዚአብሔር፡ ተገዙ። ሰይጣንን፡ ተቋቋሙ፡ ከላንትም፡ ይሸሻል።

፰፥ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ቅረቡ፡ እርሱም፡ ወደላ ንት፡ይቀርባል።

## ወደ፡ ዕብራውያን። ፪፥

፲፬፥ ልጆችም፡ በሥጋና፡ በደም፡ ተገናኝተውታልና፡ እርሱም፡ ደግሞ፡ በዚህ፡ ተገናኘው፡ በሞቱ፡ የ ሞት፡ ሥልጣን፡ ያለውን፡ ይሽር፡ ዘንድ፡ እርሱም፡ ሰይጣን።

## ፩፥ ዮሐንስ፡ ፫፥

፰፥ ኃጢአትም፡ የሚያደርግ፡ እርሱ፡ ከሰይጣን፡ ነው፡ ሰይጣን፡ ከጥንት፡ ኃጢአትን፡ አድርጓልና። ስለ ዚህ፡ተገለጠ፡ የእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ የሰይጣንን፡ ስ ራ፡ ሊሽር።

## ወደ፡ ተሰሎንቄ፡ ሰዎች፡ ፪፡፡ ፪፥

፰፥ የዚ የን፡ ጊዜ፡ ያክፉ፡ ይገለጣል፡ ጌታችን፡ ባፉ፡ መንፈስ፡ የሚያጠፋው፡ በመምጣቱም፡ መገለጥ፡ ከንቱ፡ያደርገዋል።

ፍቅር፤ የሻቀመዛመዱትነት፡ፈተና።

፩፡ ዮሐንስ። ፬፡

፳፡ እግዚአብሔርን፡ እወደዋለሁ፡ ብሎ፡ ወንድሙን፡ የሚጸላ፡አሰተኛ፡ነው። ያየውን፡ ወንድሙን፡ ያልወደደ፡ ያላየውን፡እግዚአብሔርን፡ ይወድ፡ዘንድ፡ እንዴት፡ ይችላልና።

ወደ፡ ገላትያ፡ ሰዎች። ፭፡

፳፪፡ የመንፈስ፡ ፍሬ፡ግን፡ ፍቅር፡ነት፡ ደስታም፡ ሰላምም ፡ ትዕግሥትም፡ ቸርነትም፡ በጎነትም፡ ሃይማኖትም፡ ገርነትም፡ መሻትንም፡ መግዛት።
፳፫፡ በዚኽ፡ተይዘው፡በሚኖሩ፡ሰዎች፡ ላይ፡ ሕግ፡ የለባቸውም።

የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፲፫፡

፴፭፡ በዚህ፡ያውቃል፡ሰው፡ሁሉ፡እላንት፡ደቀ፡መዛሙርቴ፡እንደ፡ሆናችሁ፡እርስ፡ በርሳችሁ፡ ፍቅር፡ ቢኖራችሁ።

ወደ፡ ቆሮንቶስ፡ ሰዎች፡ ፩። ፲፫፡

፩፡ በሰዎችና፡ በመላእክት፡ ቋንቋ፡ ብናገር፡ ፍቅርም፡ባትኖርብኝ፡እንደሚጮህ፡ ናስ፡ ሆንሁ። ወይም፡ እንደሚጮህ፡ ጸናጽል።

# የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ትንሣኤ ::

## የሐዋርያት፡ ሥራ። ፲፡

፴፱፡ እኛም፡ምስክሮች፡ነን፡ ባደረገው፡ነገር፡ሁሉ፡ በይሁዳ፡ሀገር፡በየሩሳሌምም።ይህን፡የገደሉት፡ በእንጨት፡ ላይ፡ ሰቅለው።

፵፡ ይህነን፡እግዚአብሔር፡ አስነሣው፡ በሶስተኛ፡ ቀን፡ ሰጠውም፡ ይገለጥ፡ ዘንድ።

፵፩፡ ለሕዝብ፡ሁሉ፡አይደለም፡ለምስክሮች፡እንጂ፡ እግዚአብሔር፡ አስቀድሞ፡ ለመረጣቸው። እኛም፡ነን፡ከርሱ፡ጋራ፡የበላን፡የጠጣንም፡ ከሙታን፡ ከተነሣ፡ በኋላ።

## የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፳፡

፳፮፡ ከስምንት፡ ቀንም፡በኋላ፡ደቀ፡መዛሙርት፡ ደግሞ፡ በውሥጥ፡ ነበሩ፡ ቶማስም፡ ከርሳቸው፡ጋራ። የሱስም፡ መጣ፡ ደጁም፡ ተቈልፎ፡ ነበር። በመካከልም፡ ቆመ፡ አለም። ሰላም፡ ለላንት፡ ይሁን።

፳፯፡ ቶማስንም፡ አለው። ጣትህን፡ ወዲህ፡ አምጣ፡ እጆችንም፡ እይ። እጅህንም፡ አምጣና፡ ወደ፡ ጐኔ፡ አግባት። ያላመንህም፡ አትሁን፡ ያመንህ፡ እንጂ።

፳፰፡ ቶማስም፡ መለሰ፡ አለም። ጌታዬ፡አምላኬም።

ትንሣኤ፡ ትልቁ፡ ተስፋችን።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፮፡

፫፡ ወይስ፡ አታውቁምን፡ እኛ፡ በየሱስ፡ ክርስቶስ፡
የተጠመቅነ፡ በሞቱ፡ እንደ፡ ተጠመቅነ።
፬፡ እንግዲህ፡ በጥምቀት፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ ተቀበርነ፡ ለ
ሞት፡ ክርስቶስ፡ ከሙታን፡ እንደ፡ ተነሣ፡ በአብ፡ ክብ
ር፡ እንደሁ፡ እኛም፡ ደግሞ፡ ባዲስ፡ ሕይወት፡ እንሔ
ድ፡ ዘንድ።
፭፡ ክርሱም፡ ጋራ፡ የተተከልነ፡ ከሆነ፡ በሞቱ፡ ምሳ
ሌ፡ እንደሁም፡ ደግሞ፡ እንሆናለን፡ በትንሣኤው።

## የዮሐንስ፡ ወንጌል። ፭፡

፳፭፡ እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ጊዜ፡ እንድ
ትመጣ፡ እርሷም፡ ዛሬ፡ አሁን፡ የእግዚአብሔርን፡
ልጅ፡ ቃል፡ የሚሰሙበት፡ የሰሙትም፡ ይድናሉ።
፳፰፡ በዚህ፡ አታድንቁ። ጊዜ፡ ትመጣለችና፡ በመ
ቃብር፡ ያሉት፡ ሁሉ፡ ቃሉን፡ የሚሰሙባት።
፳፱፡ ይወጡማል፡ መልካምም፡ የሰሩ፡ ወደ፡ ሕይወ
ት፡ ትንሣኤ፡ ክፉም፡ የሰሩ፡ ወደ፡ ፍርድ፡ ትንሣኤ።

## ቅዳሴና፡ለጌታችን።

### ወደ፡ ቆሮንቶስ፡ ሰዎች፡ ፪፡ ፯፡

፩፡ እንደሀ፡ያለ፡ተስፋ፡ካለን፡ወዳጆቼ፡ሆይ፡ሰው
ነታችንን፡እናጽራ፡ከሥጋንና፡ከነፍስ፡ርኩሰት፡ሁሉ፡ቅ
ድስናን፡ በመፈጸም፡ እግዚአብሔርን፡ ኢየፈራን።

### ፩፡ ጴጥሮስ። ፩፡

፲፭፡ ነገር፡ ግን፡ እንደ፡ ጻራችሁ፡ እንደ፡ቅዱሱ፡ እላ
ንት፡ደግሞ፡ ቅዱሳን፡ ሁኑ፡በአካሔዳችሁ፡ ሁሉ።

### ወደ፡ ዕብራውያን። ፲፫፡

፲፪፡ስለዚህም፡የሱስ፡ ሕዝቡን፡ በደሙ፡ ሊያነጻ፡
ካገር፡በዐዊደ፡ ሕማማት፡ተቀበለ።

### ፩፡ ዮሐንስ፡ ፩፡

፱፡ በኃጢአታችን፡ ብንናዘዝ፡እርሱ፡ ተየታመነና፡
ጻድቅ፡ነው፡ኃጢአታችንን፡ይቅር፡ይልን፡ ዘንድ፡ከግፍ
ም፡ ሁሉ፡ ያነጻን፡ ዘንድ።

### ወደ፡ ኤፌሶን፡ ሰዎች። ፩፡

፬፡ በርሱ፡እንደ፡ መረጠን፡ዓለም፡ሳይፈጠር፡ ቀ
ደሳን፡እንሆን፡ዘንድ፡በፊቱ፡ያለ፡ነውርም፡በፍቅር።

# በመንፈስ፡ የተሞሉ፡ ሰዎች ።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፰፡

፱፡ እናንተ፡ግን፡በሥጋ፡አይደላችሁም፡በመንፈ
ስ፡እንጂ፡የእግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ቢያድርባችሁ።
የክርስቶስ፡መንፈስ፡ግን፡የሌለበት፡ያ፡እርሱ፡ለርሱ፡
አይደለም።

## የሐዋርያት፡ ሥራ። ፲፫፤

፶፪፡ ደቀ፡ መዛሙርትም፡ ደስታን፡ መንፈስ፡
ቅዱስንም፡ መሉ።

## ትንቢተ፡ ሕዝቅኤል። ፴፮፤

፳፯፤ መንፈሴንም፡ በውሥጣችሁ፡ እሰጣለሁ፡ በ
ትእዛዜም፡ እንድትሔዱ፡ አደርጋለሁ፡ ፍርዴንም፡
እንድትጠብቁ፡እንድታደርጒትም።

## የሐዋርያት፡ ሥራ። ፩፤

፰፤ ነገር፡ግን፡ኃይል፡ትቀበላላችሁ፡ መንፈስ፡ቅዱ
ስ፡ በወረደባችሁ፡ ጊዜ። ለኔም፡ ትመሰክራላችሁ፡

## የሐዋርያት፡ ሥራ። ፬፤

፴፩፤ በለመኑም፡ጊዜ፡ተከማችተው፡የነበረበት፡
ስፍራ፡ተናወጠ። ሁሉም፡ መንፈስ፡ቅዱስን፡መሉ፡የ
እግዚአብሔርንም፡ነገር፡በድፍረት፡ተናገሩ።

# አስፈላጊ፡ ቃልኪዳኖች፡ ለክርስቲያኖች ::

## መዝሙር:: ፴፬፡

፲፰፡ እግዚአብሔር፡ ልባቸው፡ ለተሰበረ፡ ቅርብ፡ ነው፡ በመንፈሳቸው፡ የተሰበሩትንም፡ ያድናቸዋል።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል:: ፮፡

፴፫፡ የእግዚአብሔርን፡ መንግሥት፡ ጽድቁንም፡ አስቀድማችሁ፡ እሹ፡ እንጂ፡ ይህም፡ ሁሉ፡ ይጨመርላችኋል።

## መዝሙር:: ፴፯፡

፫፡ በእግዚአብሔር፡ እመን፡ በጎም፡ አድርግ። በምድር፡ ተቀመጥ፡ ታምነኽም፡ ትሰማራለህ።
፬፡ በእግዚአብሔር፡ ተድላ፡ አድርግ፡ የልብኽም፡ መሻት፡ ይሰጥኻል።

## ፩፡ ጴጥሮስ፡ ፬፡

፲፪፡ ወዳጆቼ፡ ሆይ፡ የምትመጣባችሁን፡ መከራ፡ እንደ፡ እሳት፡ የምትሆንን፡ እንግዳ፡ እንደ፡ልዩ፡ ስ ራ።

፲፫፡ ነገር፡ግን፡በክርስቶስ፡ሕማም፡አንድ፡በመሆናችሁ፡ደስ፡ ይበላችሁ። ክብሩ፡ በተገለጠ፡ጊዜ፡ እጅግ፡ ደስ፡ ይላችሁ፡ ዘንድ፡ደግሞ።

ፈተና፡ ለገጠመው፡ ቃልኪዳን።

ወደ፡ ዕብራውያን። ፪፡

፲፰፡ ሕማማት፡ በተቀበለበትና፡ በተፈተነበት፡ ነገ
ር፡ እርሱ፡ የተፈተኑትን፡ ያግዝ፡ ዘንድ፡ ይችላልና።

ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፲፮፡

፳፡ እግዚአብሔርም፡ የሰላም፡ አምላክ፡ ሰይጣ
ንን፡ ከግራችሁ፡ በታች፡ ፈጥኖ፡ ይቀጥቅጠው።

መዝሙር። ፴፬፡

፲፱፡ የጻድቅ፡ መከራው፡ ብዙ፡ ነው። እግዚአብ
ሔርም፡ ከሁሉ፡ ያድነዋል።

ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፰፡

፳፰፡ ፈጽመንም፡ እናውቃለን፡ እግዚአብሔርን፡
የሚወዱን፡ ሰዎች፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ያግዛቸዋል፡ መልካ
ም፡ እንዲሆንላቸው፡ ለተጸራቸው፡ በፈቃዱ።

ወደ፡ ቆሮንቶስ፡ ሰዎች፡ ፩። ፲፡

፲፫፡ ሌላ፡ ፈተና፡ አላገኛችሁም፡ እንደ፡ ሰው፡ ያለ፡
ፈተና፡ እንጂ። እግዚአብሔር፡ ግን፡ እውነተኛ፡ ነው፡
አይተዋችሁም፡ ትፈተኑ፡ ዘንድ፡ በማትችሉት። ነገር፡
ግን፡ ከፈተናችሁ፡ ጋራ፡ መውጫውን፡ ያደርግላችኋ
ል፡ ታገሡ፡ ዘንድ፡ እንድችሉ።

# ላሸናፊዎች፡ ቃል፡ ኪዳን።

## የዮሐንስ፡ ራእይ። ፫፤

፭፤ ድል፡የነሣ፡ይህ፡ ነጭ፡ልብስ፡ይለብሳል። ስሙ
ንም፡ ከሕይወት፡ መጽሐፍ፡ አላጠፋውም፡ ስሙ
ንም፡ እምነበታለሁ፡ ባባቴ፡ ፊት፡በመላእክቱም።

## የዮሐንስ፡ ራእይ። ፳፩፤

፯፤ ድል፡ የነሣ፡ ሁሉን፡ ይወርሳል። እኔም፡ አም
ላክ፡ እሆነዋለሁ፡ እርሱም፡ ልጅ፡ ይሆናል።

## የዮሐንስ፡ ራእይ። ፪፤

፯፤ ጆሮ፡ ያለው፡ ይስማ፡ መንፈስ፡ ለአብያተ፡ ክር
ስቲያናት፡የሚለውን። ድል፡ ለነሣው፡ እኔ፡ እሰጠዋ
ለሁ፡ ይበላ፡ ዘንድ፡ በእግዚአብሔር፡ ገነት፡ ውስጥ፡
ካለው፡ ከሕይወት፡ ዛፍ።

## የዮሐንስ፡ ራእይ። ፫፤

፳፩፤ ድል፡ለነሣው፡እሰጠዋለሁ፡ከኔ፡ጋራ፡ይቀመ
ጥ፡ዘንድ፡ በዙፋኔ፡ላይ። እኔ፡ ደግሞ፡ ድል፡እንደ፡ነሣ
ሁ፡ካባቴም፡ ጋራ፡ እንደ፡ ተቀመጥሁ፡ በዙፋኑ፡ላይ።

# እግዚአብሔር፡ ስለመፋታት፡ ይነግረናል።

## የሉቃስ፡ ወንጌል። ፲፮፡

፲፰፡ ምሽቱን፡የፈታ፡ ሁሉ፡ ሌላዪቱንም፡ ያገባ፡ እርሱ፡ያመነዝራል። ከባልዋም፡ የተፈታቸውን፡ ያገባ፡ ሁሉ፡እርሱ፡ያመነዝራል።

## ወደ፡ ሮሜ፡ ሰዎች። ፯፡

፪፡ ሴት፡በሕግ፡ለባልዋ፡ታሥራ፡ትኖራለችና፡ባለበቱ፡ዘመን። ባልዋ፡ግን፡ከሞተ፡ በኋላ፡ አርነት፡ ትወጣለች፡ ከባልዋ፡ ሕግ።

፫፡ ባልዋም፡ በሕይወቱ፡ሳለ፡ ብታገባ፡ አመንዝራ፡ ትባላለች፡ ለሌላ፡ ወንድ፡ ብትሆን። ባልዋ፡ ግን፡ከሞተ፡በኋላ፡ከሕግ፡አርነት፡ወጣች፡ አመንዝራም፡አትባልም፡ ለሌላ፡ ወንድ፡ብትሆን።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፭፡

፴፪፡ እኔ፡ግን፡እላችኋለሁ። ምሽቱን፡የፈታ፡ሁሉ፡ ያለ፡ ዝሙት፡ምክንያት፡ እርሱ፡ አመንዝራ፡ አደረጋት። የተፈታችውንም፡ ያገባ፡ አመነዘረ።

# የክርስቶስ፡ዳግመኛ፡መምጣት፡፡

## የማቴዎስ፡ ወንጌል፡፡ ፳፬፡

፳፯፡ መብረቅ፡ ከምሥራቅ፡ እንደ፡ወጣ፡ እስከ፡ ምዕራብም፡ እንደ፡ታየ፡ እንደሁ፡ደግሞ፡ የሰው፡ ልጅ፡ መምጣቱ፡ ይሆናልና፡፡

## የማቴዎስ፡ ወንጌል፡፡ ፳፬፡

፴፡ የዚያን፡ ጊዜም፡ የሰው፡ ልጅ፡ ምልክት፡ በሰማይ፡ይገለጣል፡፡ የዚያን፡ ጊዜም፡ ያለቅሳሉ፡የምድር፡ አሕዛብ፡ ሁሉ፡፡ የሰው፡ልጅም፡ በሰማይ፡ ደመና፡ ላይ፡ ሲመጣ፡ ያዩታል፡ ከኃይልና፡ ከብዙ፡ ምስጋና፡ ጋራ፡፡

## ፩፡ ዮሐንስ፡ ፫፡

፪፡ ወዳጆቼ፡ ሆይ፡ እኛ፡ አሁን፡ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ነን፡፡ ገናም፡ምን፡እንሆናለን፡ አልተገለጠም፡ ነገር፡ግን፡ እርሱ፡ በተገለጠ፡ጊዜ፡ እንደርሱ፡ እንድንሆን፡አወቅን፡፡ እናየዋለንና፡ እርሱ፡ እንዳለ፡፡

## የዮሐንስ፡ ወንጌል፡፡ ፲፬፡

፫፡ በሔድሁም፡ ቦታም፡ ባዘጋጀሁላችሁ፡ ጊዜ፡ ደግሞ፡እመጣለሁ፡ወደኔም፡እወስዳችኋለሁ፡፡ እኔ፡ወዳለሁበት፡ እላንትም፡ደግሞ፡ ትሆኑ፡ ዘንድ፡፡

### የሉቃስ፡ ወንጌል። ፲፪፤

፵፤ እላንትም፡ደግሞ፡የተዘጋጃችሁ፡ሁኑ።የሰው፡
ልጅ፡ ባልጠረጠራችሁት፡ ቀን፡ ይመጣልና።

### የሉቃስ፡ ወንጌል። ፳፩፡

፳፯፡ የዚያን፡ጊዜም፡የሰው፡ ልጅ፡ በደመና፡ ሲመ
ጣ፡ ሃያል፡ ከታላቅ፡ ኃይል፡ ከክብርም ፡ ጋራ።

### የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፲፮፡

፳፯፡ የሰው፡ ልጅ፡ ይመጣልና፡ ባባቱ፡ ክብር፡ ከመ
ልክተኞቹ፡ ጋራ። የዚያን፡ ጊዜም፡ ለሁሉ፡ ፍዳውን፡
ይሰጣል፡ እንደ፡ ስራው።

### የዮሐንስ፡ ራእይ። ፲፮፤

፲፭፤ እነሆ፡ እኔ፡ እንደ፡ሌባ፡ እመጣለሁ። የሚተ
ጋ፡ ብፁዕ፡ ነው፡ ልብሱንም፡ የሚጠብቅ፡ ራቁቱን፡
እንዳይሔድ፡ ኃፍረቱንም፡ እንዳያዩ።

### የሐዋርያት፡ ስራ። ፩፤

፲፩፤ ሲልዋቸውም። እላንት፡የገሊላ፡ ሰዎች፡ለም
ን፡ ቁማችኋል፡ ወደ፡ ሰማይ፡ እያያችሁ። ይህ፡ የሱ
ስ፡ ከላንት፡ ወደ፡ ሰማይ፡ የወጣው፡ እንደሁ፡ ይመ
ጣል፡ እንዳያችሁት፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ሲወጣ።

የእግዚአብሔር፡ ቃል።

## ፪፡ ጴጥሮስ፡ ፩፤

፳፩፤ ትንቢት፡ከቶ፡ በሰው፡ ፈቃድ፡ አልመጣችምና፡ነገር፡ግን፡ ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ተመርተው፡ የእግዚአብሔር፡ቅዱሳን፡ ሰዎች፡ ተናገሩ።

## መዝሙር። ፻፲፱፤

፲፩፤ አንተን፡ እንዳልበድል፡ ነገርኽን፡ በልቤ፡ ሰወርሁ።

## ወደ፡ ጢሞቴዎስ፡ ፪፡፤ ፫፡

፲፮፤ መጽሐፍ፡*ሁሉ፡ በእግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ተጻፈች፡ ለትምህርትም፡ ትረባለች፡ለዘለፋም፡ ለተግሣጽም፡ ለማስተማርም፡ በጽድቅ።

## መዝሙር። ፻፲፱፤

፻፭፤ ሕግኽ፡ ለግሬ፡ መብራትና፡ ለመንገዴም፡ ብርሃን፡ነው።

## የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፳፪፤

፳፱፤ የሱስም፡መለሰ፡ አላቸውም። ሳታችሁ፡ መጽሐፍ፡ ባለ፡ ማወቅ፡ የእግዚአብሔርንም፡ ኃይል።

Published in numerous languages by World Missionary Press as God supplies funds in answer to prayer. Other booklets are also available. If you would like more copies for careful distribution, write in English to:

World Missionary Press, Inc.
P.O Box 120
New Paris, Indiana 46553-0120 USA

Ethiopia

AMH

142 Amharic